**የመጨረሻው ሰይጣን**
**አዲስ አበባ**

**ከበልጅግ አሊ**

ባለፉት የመጨረሻው ሰይጣን ከሚለው ታሪክ ውስጥ እውን ኢሕአፓ መሆን ያኮራል የሚለውን በተከታታይ ሳቀርብ እንደነበርኩ ይታወሳል።ለተወሰነ ግዜ ያቋረጥኩትን ይህን ታሪክ አሁን እንደገና እጀምራለሁ። ከመጀመሪያው ክፍል እስቲ አንዳንዶቹን እናስታውስ።

በመጀመሪያው ክፍል አንድ በጨካኝነቱ፣ በገራፊነቱ ፣ በገዳይነቱ፣ ይታወቅ የነበረ ግለሰብ የደርግ መንግስት ከወደቀ በኃላ በቤተሰቦቹና በእሱ ላይ የደረሰበትን ችግር አንድ ኢሕአፓ ለነበረ በቀይ ሽብር ወቅት አስሮ ላሰቃየው በውጭ የሚገኝ የቀድሞ ጓደኛው  ፅፎ እርዳታ ስለጠየቀው የገንዘብ እርዳታ ያደርግለት ነበር። ይህም ጨካኝ የሰራውን ሁሉ ግፍ ፅፎ ከሰጠው በኃላ እራሱን ያጠፋል። በኑዛዜውም ላይ እኔ ከሞትኩኝ በኃላ ታሪኬን ልትፅፈው ትችላለህ ብሎ በፈቀደለት መሰረት ታሪኩን አንድ የሌላ ጓደኛው እናት ልጃቸውን ሊጠይቁ እሱ አለበት አገር ስለመጡ ከእርሳቸው ጋር በሚወያይበት ግዜ አንስተውበት ታሪኩን ይተርክላቸዋል። እስቲ አንዳንዶቹን ወይይቶች እናስታውስ።

- እንደምን ከረሙ እናቴ? ደህና ከርሙ?
- ደህና ነኝ። ምን እሆናለሁ ብለህ ።
- ማንበብ ጀመሩ ኑዛዜውን?
- አነበብኩት እንጂ ልጄ፣ አነበብኩት፣ አየኸው ያለውን ።

በአለም ላይ ታላላቆቹ ጨካኞች እንኳን ሳይቀሩ አንድ ቀን ህፃን እንደነበሩና የእናት ፍቅር እንደሚያስፈልጋቸው ልትረዱት ይገባል ነው እኮ የሚለን ልጄ። መቼ ይለያያል ብለህ የልጅ ፍቅር ፣ የእናት ፍቅር ፣ የአገር ፍቅር ፣ ሁሉም እኮ አንድ ነው። ከአለእናት ማደጉን አየሁት፣አነበብኩት። ልጄ የእናት ጡት እኮ ነው ሰውን ከአውሬነት ወደ ሰውነት የሚለውጥ ይባላል። እናትኮ ነች ለሁሉም መድሃኒት። አይ ልጄ ምን ያድርገው ብለህ።

ቢያጣ እናቱን ቢሻ ፍቅሯን
ቢናፍቅ ሽታዋን አንድ እናቱን
ቢያልም የማያውቃትን ።
ፍቅሩዋን ፤ ሳትሰጠው ጥላው የሄደችው
እየወደደችው።

እሱስ አላየኸውም እንዴ በስተመጨረሻው እኮ እናት ፍቅር ነች አለ፡ጨካኝም ህፃን ነበር ይበል። ከአለ እናት ማደጉን ልቡ ውስጥ ከርሞ አንገብግቦት። አንተስ ትርሳው ይሆን ብዬ አላስብም። ያኔ በዛ በዶፍ ዝናብ ጥቁር ባለ ቀን እነዚያ ባንዳዎች

እጅህን በእግር ብረት ጠፍረው ሲወስዱህ
እናትህ የሆኑትን እስክትፈታ ታስረህ።
አንድ ጋቢ ላይ፤ደረቁ መሬት ላይ፡የተኙትን

ጠዋት ማታ ተንበርክከው የፀለዩትን
ጌታዬ የልጄን እሬሳ አታሳየኝ ያሉትን
በማለዳ እሬሳ የዳበሱትን የፈለጉትን።

እንዴት ልጄ ከባድ መሰለህ
ልብህ ሆድህ ውስጥ ሲንቦጫቦጭብህ
ያ ከመሀፀንህ የወጣው ልጅህ
መንገድ ወድቆ በደም ተጨማልቆ
ማግኘት መቻልህን ማወቅህ ።

በውይይታቸው መሃል እሳቸውም የአካባቢው ህዝብ ስለ ኢሕአፓ ያለውን አመለካከት ይነግሩታል። አንድ ወንድ ልጃቸው በቀይ ሽብር የተመታባቸው ሲሆን አንዱ ደግሞ ከአስራ ሰባት አመት ስደት በኃላ ተመልሶ መጥቶአል። ከስደት ከተመለሰ በሁዋላ በቀይ ሽብር የተመታችበትን እጮኛውን አስከሬን አግኝቶ እንደገና እንድትቀበር አድርጓል። ይህ በስደት የነበረው ልጃቸው አሁን ታሪኩን ከሚተርክላቸው ጋር የቅርብ ጓደኞች እንደነበሩ ቢያውቁም አሁን ግን እሳቸው በማያውቁት ነገር ተቀያይመው ስለነበር ሁለቱን ለማስታረቅ ሞክረው ተሳክቶላቸው ሁለቱም ደብዳቤ መፃፃፍ ጀምረዋል። እስቲ ከደብዳቤዎቹ መካከል አንዱን እንመልከት። ይህንን የተናገሩት አባቱ ሲሆኑ ለመጨረሻ ግዜ በተለያዩበት ወቅት ነው።

„ አንተ ከዛሬ ጀምሮ ለኛ የሞትክ ነህ ። ቅዳሜ በቀይ ሽብር እንደተመታህና እሩቅ ሰፈር ወድቀህ እንደተገኘህ ተደርጎ መርዶ እንቀመጣለን። የሚያረዱንም ሰዎችም ተዘጋጅተዋል። አንተም ከዚህ ጥፋ እንዳትገኝ ማምለጫ መንገድ ከሌለህ እኛ እናግዝሃለን። ከሽማግሌው ጋር ተወያይተን ነው የወሰነው እናትህ አዘኑ እንደሚጎዳት እናውቃለን። ቢሆንም ነገሩን ለማሳመን እናትህ አለመስማትዋን አምነንበታል። የገደልንህ አንተን ለማዳን ስለሆነ ሞትህን በደስታ ተቀበለው። እኛን ለማግኘት ብለህ የብዙዎቻችንን ህይወት አደጋ ላይ እንደማትጥል እተማመንብሃለሁ። አንተም ደግሞ እራስህን ጠብቅ። አካባቢህን ለመምሰል አትሞክር። አንዳንድ ጊዜ አካባቢ ሞኝ ነውና አካባቢን መምሰል ሞኝነት ይሆናል። ጊዜ ያልፋል እስከሚያልፍም ያለፋል። ምን አይነት ኑሮ የሞተ ሰው እንደሚኖር አላውቅምና ምንም ልመክርህ አልችልም። እግዚሃብሔር ከፈቀደ ወደ ፊት ትነግረኛለህ። ችግር እንደሚገጥምህ አልጠራጠርም። የሆነ ሆኖ እንደ ጓደኛህ ችግሩን ወደ ሌላ እንደማታስተላልፍ አምናለው። ጓደኛህ በሀዘን ውስጥ ደስታን ለቤተሰቦቹ ሰጥቶሰቸዋል። ልጃችሁ ልጃችንን እንዲገደል አደረገብን የሚላቸው አይኖርም። አንተም እኛን ሽማግሌዎቹን በስተርጅና ቀባሪ አታሳጣንም ብዬ አምናለሁ። ብዙ ምስጢር ታውቅ ይሆናል ልጄ ያንንም ያመንክበት ስለሆነ ጠብቀው። በቆራጥነትህ በአላማህ ፅናት እንደምትከበር እንዳትጠራጠር። በትንንሽ ሁኔታ አሳብህን ለመቀየር እንዳትሞክር። ምክንያቱም በጊዜያዊ ሁኔታ እንዳትደለል ወይም እንዳታመነታ እፈልጋለሁ። ትንንሽ ድሎች መጨረሻ ላይ ሊቀየሩ ይችላሉ“።

ባለፈው ታሪኩ የቆመው የመጨረሻው ሰይጣን በመባል የታወቀው ጨካኙ ግለሰብ አስተዳደጉን በኑዛዜው ላይ ከገለፀልን በኋላ ነው። የጨካኙ ሰው አባት የጨካኙን ሰው እናት ለማግባት በመፈለግ ግን ደግሞ ስላልተሳካለት የጨካኙን እናት አባት ገድሎ ጫካ ገብቶ ነበር። ከዛም ተታርቆ ገንዘብ ከፍሎ ከገባ በኃላ የጨካኙን እናት ሊያገባ ችሎአል። አባትየው ልጁን እንዴት እንዳሳደገው በአለፈው ተጠቅሷል። ታሪኩ የቆመው

አባትየው ሞቶ እቀብሩ ላይ ከተገኘ በኃላ አንቱ ወደ አዲስ አበባ ሲወስደው ነው። ለማስታወስ ያህል በመጨረሻ ስለ አባቱ የተገጠመውን እናንብ ።

ጋብቻ ቢጠይቅ አባት እንቢ ቢለው
የተጠጋው ጋኔል ግደል ግደል ሲለው
ሰውሮበት ኖሮ ደም መላሽ እንዳለው
አባቷን በጥይት ገድሎ አሳረፈው ።

የአገር አጉራ ዘለል የሰፈር ወንበዴ
አግብቶ አሳያቸው ልጅቱን በዘዴ
ወልደው ከብደው ሳለ ሞቆ ትዳራቸው
ደሙ ፀዳ ብለው በመዋለዳቸው
አማቹ ይገለኛል ብሎም አልጠበቀ
የሚች ልጅ አደገ ቂም እንደጠበቀ
ደም በደም ነውና ወትሮም የሚፀዳው
ልጅየው በተራው አማቹን ገደለው
ደም ይበቀል ይሆን የሚች ልጅ በተራው።

ገዳዩ አንቱ የሞተው አባቱ
አንቱን ቢገድለው ምን አለው እንጀቱ
ለመከራ የጣፈው የጠዋት እድሉ
ሃዘኑ ቅጥ አጣ አለወጣም ከልቡ ።

ታሪኩ ያቆምኩት እዚህ ላይ ነበር። የመጨረሻው ሰይጣን አዲስ አባበ ገብቶ እንዴት አገኘው። እንዴትስ ወደ ጨካኝ ተግባሮቹ ሄደ ምን ምንስ አደረገ። በስደት የነበረው ጓደኛው ኑሮው እንዴት ነበር። በቀይሽብር የተመተችውን ጓደኛውን እንዴት አገኛት። በሚቀጥለው ተከታታይ ታሪክ ስለሚቀርብ ተከታተሉት።

የመጨረሻው ሰይጣን
ክፍል 7

# አዲስ አበባ

አዲሰ አበባን እንደጠበቅሁት አላገኘሁትም ። ገና አገሬ እያለሁ ሰለ አዲስ አበባ ሲወራ በመደነቅ ነበር ሁሉን ነገር የምሰማው። መቼ ይሆን ይህንን አገር የማየው ብዬ ያላሰብኩበት ቀን ይኖራል ብዬ አላምንም። ገና አውቶቡሱ እየቀረበ ሲመጣ ልቤ ፈራ ተባ ማለት ጀመረ። ምን እንደሚገጥመኝ አላቅም። ሰዎች ሲያወሩ የሰማሁት ሁሉም የሚያስፋራ ነበር። አዲስ አበባ ግን በመጀመሪያ ከአውቶብሱ ስወርድ ማንም ማንንም የማያዳምጥበት ጫጫታ ነው ሆኖ ያገኘሁት። ለኔ ያኔ አዲስ አበባ.........

አወቶበስ ተራ፣ ጫጫታ፣ ጨኸት ፣ የመኪና ጡሩምባ ፣ በራሪ፣ ሎንችና፣ ቲኬት፣ ትኬት ቀራጭ፣ሾፌር፣

- እቃውን እላይ አወጣው፣
- ጫነው፣አውርደው፣
- አይን የለህም፣
- አይን የለሽም፣
- አትጋፋ፣
- አትጋፊ፣

ጥድፊያ፣ሁካታ፣የገጠር ሰው፣የከተማ ሰው፣ ሌባ፣ኡኡ፣ያዘው፣መንታፊ፣ቁማር፣ይህችን ያወቀ ይህንን ይበላል፣ ጓደኛሞች ፣ ማታለል ፣ መስረቅ፣ ያዘው፣ሌባ፣መሯሯጥ፣ አፍ መክፈት፣ ወሬ ማየት፣ መሰረቅ፣ በተራ መጮህ፣ከአውቶቢስ ላይ ሙዚቃ ፣ልቤን ገልጠሽ እይው የግልሽ ነው፣በመጠጥ ደሰታ፣ ተማር ልጄ፣የሺ ሀረጊቱ፣ እዚህ ተቀመጪ፣ ተነስ፣ውረድ፣የኔ ቦታ ነው፣ጠጋ ጠጋ ብላችሁ ተቀመጡ፣ቦታ መምረጥ፣ወጣት ከወጣት፣ሽማግሌ ከአሮጊት፣

- ትኬት፣ስንት ነው፣
- አስር ብር፣
- ስምንት አደለም እንዴ ?
- በራሪ ነው፣ውረድ፣ውጣ፣
- ገንዘብ፣ገንዘብ ፣ገንዘብ ።
- ኩሊ፣ኩሊ፣ኩሊ፣
- እስከ ታክሲ ድረስ፣
- ሁለት ብር፣
- ለዚች፣ቀላል
- ከሆነ እራስሽ ተሸከሚው፣
- ኩሊ፣ኩሊ፣ኩሊ፣
- እስከ ታክሲ ድረስ፣
- ሶስት ብር ፣
- በል ተወው፣
- በል አንተ ና ወሰደው፣ሁለት እከፍላለሁ፣
- አልወስድም፣ሶስት ብር፣
- ሁለት አላልክም እንዴ፣
- አሁን ተወደደ፣
- አሁን በአሁን፣
- አንቺ ስታማርጪ ሲዌዝ ካናል ተዘጋ፣
- በል ና ውሰደው ልጄ፣ ሆፕ ላስ፣ መጫን፣መወሰድ፣ማራገፍ።

ታክሲ፣ ታክሲ፣ታክሲ፣ ሲሸንቶ፣ ሰማያዊ ፊያት፣አንድ ሰው ለገሃር፣ ልደታ፣ፒያሳ፣ አብነት፣ሜክስኮ፣ካዛንችስ፣እስታዲዮም፣ቦሌ፣ቁራ፣ጎፋ፣ዶሮ ማነቂያ፣ ሰራተኛ ሰፈር፣ ቡልጋሪያ ማዞሪያ፣ጉለሌ፣ አሮጌው አውሮፐላን ማረፊያ፣ ቶታል፣አራት ኪሎ፣ስድሰት ኪሎ፣መካኒሳ፣ኮልፌ፣ መስጊድ፣ባንቢስ፣ቴዎድሮስ አደባባይ፣ገዳም ሰፈር፣ጣሊያን ሰፈር፣ አፍንጮ በር፣እሪ በከንቱ፣ቸርችል ሮድ፣ ደጎል አደባባይ፣ መስቀል አደባባይ፣ ሱማሌተራ፣ ፖፖራሌ፣ገነት ሆቴል፣ኦርማ ጋራጅ፣ተክለ ሀይማኖት፣አሰኮ ፣ዳርማር ፣ሞላ ማሩ ፣፣ገጀ ሰፈር፣፣መርካቶ፣ አደሬ ሰፈር፣ አንድ ሰው ፣ሁለት ሰው፣ከነእቃው ፣ አንድ ፣ወደ ኮሮኮንቹ አልገባም ፣እመንገድ ላይ ይበቃኛል፣ አንድ ብር ከስሙኒ፣አራት ፍራንክ፣ ሽልንግ፣እረብሻ፣እረብሻ፣የማያቆርጥ እንቅስቃሴ፣የማይበርድ ጨኸት።

ሱቅ በደረቴ፣ቆሎ፣ ቆሎ፣ ሸንኮራ፣አቾሎኒ፣በኮርኪ ሁለት ፍራንክ፣፣ሸንብራ ድቤ፣ አይገኝም በዱቤ ፣ ማስቲካ፣ከረሜላ፣ደጎል፣ደሰታ፣ኮሾ፣ የዱባ ፍሬ፣ ሲጋራ፣ትንባሆ፣ጭስ

መዋጥ፣መልሶ ማውጣት፣እረ ሰውየው ተቃጠለ ጎበዝ፣ መደነቅ፣አፍሶ መሮጥ፣ያዘው፣የደሃውን ንብረት ፣ ማስቲካ ከአክተር ፎቶ ጋር።

ሂልተን፣ዋቢ ሸበሌ፣ጊዮን፣ራስ ሆቴል፣ኢትዮጵያ ሆቴል፣ዴ አፍሪክ፣ሐራምቤ፣ ቸንትሮ፣ትሪያኖን፣ገብረ ትንሣይ፣ፍላሚንጎ፣አብነት፣ሴተኛ አዳሪ፣ሜታ ቢራ፣ጊዮርጊስ፣ መሎቲ ፣ኤልያስ ፓፓሲኖስ፣ሞላ ማሩ፣ኮካ ኮላ፣ፋንታ፣ሲሮኮ፣ጠጅ ቤት፣ጠላ ቤት፣ ፊሊተር፣መጠጣት፣መስከር፣

- አልጋ መያዝ፣
- መዳራት፣
- ይቻላል፣
- አዎ ይቻላል፣
- ሾርት፣አዳር፣
- የመሸታ ሰጋ፣
- የማይበላ ስጋ፣
- ለነፍስ ሕይወት ጊዜያዊ ደስታ፣
- ለሌላው መተዳደሪያ፣
- ዛሬም ነገም ሁሌም፣
- ሰካራም፣
- ሾርት፣ሁለት ብር፣ሶስት ብር፣
- ግብ ግብ፣
- በለወ በለው፣
- ምን ያስቸኩልሃል፣
- በደንብ ስጭኝ፣ገንዘቤ ነው፣
- ዋ ዋ ፣ኡ ኡ፣እዚህ ፣እዚያ ፣እዚህ
- የአጠና አልጋ፣የሸቦ አልጋ፣መጋረጃ፣
- በለው፣በለው፣መጮህ መጨረስ፣
- መታጠቅ ፣
- እፍይ ማለት፣መሄድ፣ሌላው መምጣት፣
- መግባት፣ግብግብ፣መሄድ፣ጨብጥ፣ቁጢኝ፣ፔኒስሊን፣ውሽማ፣አልጋ መውረጃ፣ዲቃላ፣ የማይጥም ኑሮ ።

ጉሊት፣ኩሊ፣ሊስትሮ፣ ሻይ ቤት፣ፓስቴ፣ቀሸር፣ጉራጌ፣ጎበዝ፣ሰራተኛ፣ለማኝ፣ ለማኝ፣ ሽንኩርት፣ችርቻሮ፣እንጨት ፈላጭ፣አታክልት አዙዋሪ ፣ቆርቆሮ ያለው፣ አናጢ፣ገንበኛ፣ ቀለም ቀቢ፣ ፍራሽ አዳሽ ።

ጠቅላይግዛት፣እንደራሴ፣ኤርትራ፣ትግራይ፣ወሎ፣ቤጌምድር፣ጎጃም፣ወለጋ፣ኢሉባቡር፣ከፋ፣ባሌ፣ጎሞጎፋ፣ሲዳሞ ፣አሩሲ፣ ሸዋ ፣ ሐረርጌ ፣ ጎሬ፣ አቤ ጉበኛ፣ አልወለድም፣ የተከለከለ መፀሐፍ፣ ጥላሁን ግዛው፣ስቱደንት ካውንስል፣ማርታ፣ መሬት ላራሹ፣አትንሳም ወይ፣ሪቮ፣ፋሽንሾው፣

ጥምቀት፣ታቦት፣ማጀብ፣ዘፈን፣ድብድብ፣መጨፈር፣መስቀል፣በግ፣ቅርጫ፣ዶሮ፣መኪና፣ ዚታኦ ፣ ኤነተሌ ፣ክትፎ ፣ጥሬ ስጋ፣መንቸት አብሽ ፣ በያይነቱ፣ጣመኝ ድገመኝ።

ሚኒስትሪ፣ ስድሰተኛ ክፍል፣ሚኒስትሪ፣ ስምንተኛ ክፍል፣ ማትሪክ፣ አሰራ ሁለተኛ፣ ክፍል፣ ማለፍ መደሰት፣መውደቅ ማልቀስ፣ኤ ቢ ሲ ዲ ኤፍ፣ መጥፋት፣ለመታነቅ ማሰብ፣ መገረፍ፣ምረጥ፣እውነት ውሸት በል፣ አጥቁር ፣አስተማሪ፣ኤኔታ፣ሕንድ ሚሰተር ሲንግ፣ሚስተር አብርሃም፣ ኤኔታ ጀማነህ፣ ፍቅር እስከመቃብር፣ጠቢያ።

ገብረ ትንሳይ፣ፒያሳ፣የዝነጣ መጀመሪያ፣ባቅላባ፣ ላቨር፣ ሌተር፣መጋበዝ፣ፊልም፣ አደዋ፣ አነፒር፣ሲኒማ ኢትዮጵያ፣አምባሳደር፣አገር ፍቅር፣ቀዳማዊ ሃይለ ስላሴ ትያትር፣ድራይቭ ኢን ፣ሲኒማ ራስ፣ አዲስ ከትማ፣ ሰይጣን ቤት፣ ቴክሳስ፣ ህንድ ፊልም፣ ግላድያተር፣ ላቭ እስቶሪ፣ መሳቅ ማልቀ፣ ኪሲንግ፣ ልቀቃት፣መጣልህ፣ሊገለው ነው፣አይገለውም፣አምልጥ፣ቴንፖ፣እንዳትቆርጠው፣ማፎጨት፣መጮህ፣ሸልንግ፣ሶስት ፊልም፣ ፊልም በማያውቁት ቋንቋ ማየት፣በህንድኛ መዝፈን፣ሃቲ ሜሪ ሳቲ፣ዝሆን ጓደኛዬ ነው፣ ሲጋራ፣ግስላ፣ጉሬዛ፣ኒያላ፣ ዊኒስተን፣ቫስሮይ፣ባለድመት፣አራንባ።

ገርል፣ቆንጆ፣ሚኒሰከርት፣ጭራ ቀረሸ፣የሚያምር እግር፣ የሚያሻፍድ ጭን፣ጉጥ ጉጥ ያለ ጡት፣የስሜት መምጣት፣መንገድ ላይ ፀያፍ ማሰብ፣ማቆም፣መብረድ፣ፍትሆተ ስጋ፣ጉርምስና፣በሴት መደባደብ፣ቻይና ግሩፕ፣መቅደላ፣ቅንብቢት፣ቀይ ከንፈር፣የተተኮሰ፣ ፀጉር ፧ላቨር ፧ ጥናት አለበኝ ፧ ጓደኛዬ ቤት ነው ፣የማድረው ፧ ባጥር መዝለል፣ ኪሲንግ፣ቡሩሽ፣ዲሰቨርጅን፣መደንገጥ፣ አለመነቃት፣መቀጠል፣ወር አበባ መቅረት ፣ማልቀስ፣ መተከዝ ፣መሰቀል፣በረኪና መጠጣት፣እራስ ማጥፋት፣ወልዶ መጣል፣ማስረገዝ፣መካድ፣የኔ አደለም፣ያንተ ነው፣ጠቅላት፣አግባት፣ዲቃላ፣ችግር፣ችግር፣ችግር፣እጠቀልልላለሁ፣አገባለሁ፣ ሠርግ ፣ ሃይ ሎጋ፣ አናሰገባም ሰርገኛ፣ ብር አንባር ሰበረሎ ፣ልጅ ፣ክርስትና፣ደስታ ደስታ ደስታ፣ ፊንጠዝያ።

ህዘን፣ ሙሾ አውራጅ፣ ቀብር፣ ጥቁር ልብስ፣ መርዶ፣ ፍትሃት፣ ቀብር፣ ንፍሮ፣ ቆሎ፣ እዝን ፣ እንጀራ ፣ወጥ ፣ ሳልስት ፣ ተዝካር ፣ህውልት ዮሴፍ ልደታ፣ተክለሃይማኖት፣ኡራኤል፣ጎላ ሚካኤል ፣ቀጨኔ መድህነ አለም፣ እንጦጦ፣ደብረ ሊባኖስ፣ እሳለም መስጊድ፣ ሌላም ፣ሌላም

ዘፋኝ፣የፍቅር፣የደስታ፣የህዘን፣የሚያስቅ፣የሚያስለቅስ፣ጥላሁን፣ ማህሙድ፣ አለማየሁ፣ ጌታቸው ካሳ፣ ካሳ ተሰማ ፣ሜሪ አርምዴ፣ታምራት ሞላ፣ አያሌው መስፍን ፣ ዳንስ ፧ ቲዊስት ፣ ታንጎ፣ቡጊ።

አይለመድ የለም ሁሉንም ለመድኩት፡፡

ይቀጥላል